# ሥርዓተ ክህነት

## 1/ የክህነት አመሠራረት

ክህነት የተጀመረው በመጀመሪያው ሰው በአዳም ነው ። እግዚአብሔር አምላክ አዳምን ፈጥሮ በልጅነት አክብሮ ነቢይ ካህን አድርጎ ስለሾመው በኦሪት በወንጌል ሥርዓት እስኪወሰን ድረስ ከአዳም ጀምሮ እስከ ሙሴ የነበሩ አበው በበረከት አበው ከእግዚአብሔር እየተሾሙ ትንቢትን ክህነትን ከቅዱስ መንፈስ እየተቀበሉ /እየተሾሙ/ በነቢይነታቸው ያለፈውን የሚመጣውን ሲገልጡ ሲያስተምሩ በክህነታቸው መሥዋዕት ሲያቀርቡ በጸሎታቸው አምላካቸውን ሲጠሩና ቃል በቃል ሲነጋገሩ ኖረዋል ።

አዳም ከገነት በወጣ በማግሥቱ በሠራው ኃጢአት ተጸጽቶ እያዘነና እያለቀሰ ቸርነት ምሕረት የባሕርዩ ከሆነው አምላክ ምሕረት ለመጠየቅ የመዓዛ መሥዋዕት አቀረበ ።

"ወዐጠነ አዳም ምስለ ትንሣኤ ፀሐዩ በከርቤ ወሚዓ ወሰሊክ" /ኩፋሌ 5፡1-5/ ካህን መባል በኦሪት ከመገለጹ በፊት የወልደ እግዚአብሔር ምሳሌ÷ የወንጌል ሥርዓተ ቁርባን መምህርና ሰባኪ የብፁዓን ሐዋርያት መሪና ፊት አውራሪ ሆኖ በቀራንዮ ሊያገለግል ታላቁ ካህን ሊቀ ካህናት ኢየሱስ ክርስቶስ ከመምጣቱና ለመሥዋዕት ከመቆሙ በፊት ቤተ መቅደሱን ሊጠብቅ ንዋያተ ቅድሳትን÷ ጾምን÷ ጸሎትን ተባሕትዎን፡ ድንግልናን ከዊን ሰማዕትን ሊያዘጋጅ ከእግዚአብሔር ተመርጦ የተሾመውና የተላከው ታላቁ ካህን መልከ ጼዴቅ ነው /ዘፍ. 14፡18-23 ፤ መዝ. 109፡4/ ።

ታላቁ ካህን መልከ ጼዴቅ የወልደ እግዚአብሔር ምሳሌ እንደ መሆኑ መጠን ሌዋውያን ካህናት የማይተካከሉትና የማይወዳደሩት ማዕርግ ክብሩ ምጡቅ÷ ምሥጢረ ክህነቱ ረቂቅ ስለሆነ የሌዋውያን አባት አብርሃም ሌዊ ገና በወገቡ ሳለ በረከተ ገጽ/ እጅ መንሻ/ አቀረበለት ፤ አሥራት አወጣለት ። መልከ ጼዴቅም ኅብስተ አኰቴቱን÷ ጽዋዐ በረከቱን ባርኮ÷ ቀድሶ በመስጠት አብርሃምን ባረከው ዕብ. 7፡1-14/ ።

ሙሴ ለአሮንና ለአልአዛር ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለሐዋርያት ከመስጠቱ በፊት ክህነትን በመምህራን ቡራኬ ከመንፈስ ቅዱስ ለማግኘትና ለመሾም መሠረቱና መጀመሪያው መልከ ጼዴቅ

አብርሃምን የባረከበት÷ አብርሃም ከመልከ ጼዴቅ የተባረከበት ያ ቡሩክ ሰዓት ነው /ሉቃ. 24:50 ፤ ዮሐ. 20:21-24 ፤ ዘሌ. 21:10-12/ ::

ክህነት በዘመነ ኦሪት ለሌዊ ነገድ ከተሰጠ በኋላ ሲወርድ ሲዋረድ እስከ ክርስቶስ ደርሱዋል :: ታላቁ ሊቀ ካህናት ኢየሱስ ክርስቶስ እንደ ብሉይ ኪዳን ካህናት መሥዋዕት እንስሳን ሳይሆን መሥዋዕት ደሙን ይዞ ራሱ መሥዋዕት÷ ራሱ ሠዋዒ ሆኖ ወደ መቅደስ ገብቱዋል /"ዘአዕረገ ለአቡሁ ርእሶ ዕጣነ ወመሥዋዕተ ሥመረ" ኢፍሬም በእግሩም ሐዋርያት እንዲተኩ በእንብሮተ እድ በንፍሐት ሾሞዋቸዋል/ዮሐ. 20:22-23 ፤ ሉቃ. 24:50 /

ሐዋርያትም ለተከታዮቻቸው በእንብሮተ እድና በንፍሐት እያስተላለፉ እስከዛሬ ደርሱዋል /የሐዋ /ሥ. 6:3-9፣ 14:23፤ 1ጢሞ. 1:3፣ 4-14፣ 2ጢሞ. 1:6 ቲቶ 1:5/ እስከ ምጽአትም ድረስ እንዲሁ እየተሰጠ ይቀጥላል ::

## 2/ የክህነት ሥልጣን

ክህነት ከፍ ያለ ሥልጣን አለው :: የማሠር የመፍታት ሌሎችንም የቤተ ክርስቲያን ምሥጢራት የመቀደስ የማክበር የመፈጸም ችሎታና ሥልጣን ያለው ጸጋ ነው ::

በሐዲስ ኪዳን የክህነት ሥልጣን ለሁሉ አይሰጥም በምእመናን ለተመረጡና ማስተማር ለሚችሉ ሰዎች ብቻ ነው :: ሢመተ ክህነት አይደገምም ሹመቱ የሚሰጠው በየደረጃው አንድ ጊዜ ብቻ ነው :: ከፈረሰ ይቀራል ፤ አይታደስም ፤ አይጠገንም ::

## 3/ የክህነት ተግባር

የክህነት ተግባር እግዚአብሔርንና ሰውን ማገልገል ነው :: እግዚአብሔርን ማገልገል ማለትም ካህናት መላእክትን መስለው በመዓልትና በሌሊት ለእግዚአብሔር የሚያቀርቡት ምስጋና ነው ::

ሰውን ማገልገል ማለትም ማስተማር÷ ማጥመቅ÷ ማቁረብ÷ መባረክ÷ መጠበቅ÷ መናዘዝ÷ መቀደስ÷ ማንጻት÷ ከኃጢአት መፍታት ከእግዚአብሔር ማስታረቅ÷ በሞት ለሚለዩ ጸሎተ ፍትሐት ማድረግ÷ በጠቅላላ በትምህርት በትሩፋት ክርስቶስን መስሎ አብነት ሆኖ መገኘት /ማቴ. 13:1-14 ፤ የሐ. ሥ. 6:4፣ 20:28-31 ፣ ዮሐ. 20:21-

24 ፤ 1ጢሞ. 4፡13፤ ማቴ. 16፡19 ፤ ኤፌ. 4፡11 ፤ 1ጴጥ. 5፡1-4/ ።

### 4/ ሢመተ ክህነት

ሢመተ ክህነት 3 ደረጃ አለው ። ይኸውም ዲቁና ቅስና ኤጲስ ቆጶስነት ነው ። ከዚህም በላይ ጳጳስ ፥ ሊቀጳጳስ ፓትርያርክ አለ ። እንደየማዕረጉም ሥርዓተ ሢመትና ጸሎት አለው ። ስለዚህ ሥርዓቱ እንዴት እንደ ሆነ ከዐፃዌ ኆኅት እስከ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት በሕገ ቤተ ክርስቲያን የተወሰነው ሥርዓተ ሢመት በየደረጃው እንደሚከተለው ተገልጿዋል ።

#### ሀ/ የፓትርያርክ /ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት/ ወይም የሊቀ ጳጳሳት አሹዋሹዋም ሥርዓት

ሀ/ ሊቃነ ጳጳሳት ቤተ ክርስቲያንን ለመጠበቅ ክርስቶስ የሾማቸው የሐዋርያት ተከታዮች ናቸው /የሐ. ሥ. 20፡28/ ።

ለ/ በአንድ ዘመን በአንድ ወምበር ሁለት ሰዎች አይሾሙም ።

ሐ/ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ሲሾም ሊቃነ ጳጳሳት ፥ ኤጲስ ቆጶሳት ይገኛሉ ። ይህ ሹመት ያለ ኤጲስ ቆጶሳት ጉባኤ አይደረግም ።

"የሀልዉ ኤጲስ ቆጶሳት በሢመተ ሊቀ ጳጳሳት እስመ ኢይትፌጸም ዝንቱ ዘእንበለ በሀላዌ ጉባኤሆሙ ለኤጲስ ቆጶሳት ወሀላዌ ሚጥሮጶሊስ ዘውእቱ ጳጳስ" /ፍት. መን አን. 4 ፤ ረስጣ 11/ ።

መ/ ሊቀ ጳጳሳት ያወገዘውን ጳጳስ ፥ ጳጳስ ያወገዘውን ኤጲስ ቆጶስ ፥ ኤጲስ ቆጶስ ያወገዘውን ቄስ ፥ ሳለም ከሞቱም በኋላ አይፈቱውም ። ቄስ ያወገዘውን ኤጲስ ቆጶስ ፥ ኤጲስ ቆጶስ ያወገዘውን ጳጳስ ፥ ጳጳስ ያወገዘውን ሊቀ ጳጳሳት ፥ ሊቀ ጳጳሳት ያወገዘውን ፓትርያርክ /ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት/ ሳለም ከሞቱም በኋላ ይፈቱዋል ። ሊቀ ጳጳሳት ያወገዘውን ሊቀ ጳጳሳት ፥ ጳጳስ ያወገዘውን ጳጳስ ፥ ኤጲስ ቆጶስ ያወገዘውን ኤጲስ ቆጶስ ፥ ቄስ ያወገዘውን ቄስ ሳለ አይፈቱውም ፤ ከሞተ በኋላ ግን ይፈቱዋል ። "ወኢይደሉ እምሊቃነጳጳሳት ፥ ወጳጳሳት ፥ ወኤጲስ ቆጶሳት ከመ ይፍታህ ዘአሠሮ ካልኡ ዘእንበለ እምድኅረ ሞቱ ፥ ወሊቀ ጳጳሳት ብውህ ውእቱ እምድኅረ ተከሥተ ከመይፍታሕ

ማእሠርሙ ለእሉ ኵሎሙ ሶበ ርእየ ዝክተ" /ሲኖዶስ 51/ ።

ሠ/ ሊቀ ጳጳሳት ወይም ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት የታመመ ለንደሆነ እስከሚድን÷ የታሠረ እንደሆነ እስከሚፈታ ይጠበቃል ፤ ሹመት ለሌላ አይሰጥም ፤ የማይድን ደዌ ከያዘውና ሊፈታ የማይችልበት እሥራት ከሆነ በላዩ ይሾማል፤ አይጠበቅም /ፍት. መን. አን. 4/።

ለ/ <u>የኤጲስ ቆጶሳት ሢመተ ክህነት ሥርዓት</u>

ሀ/ ኤጲስ ቆጶስ ኖላዊ /ጠባቂ/ ነው÷ /ፍት. መን. አን. 5፤ ሕዝ. 34፡1-10 ፤ ዮሐ. 10፡2-16፤ 21፡15-17/ ።

ለ/ ኤጲስ ቆጶስነት የሚሾም ነውር የሌለበት በልቡናው ከሐኬት የነቃ÷ የሚያረጋጋ÷ እንግዳ መቀበልን የሚወድ÷ የተማረ አብዝቶ የማይጠጣ ፈጥኖ የማይማታ ብልህና አዋቂ ነው ። "ወነዋ ይደሉ ከመይኩን ኤጲስ ቆጶስ ዘኢተረከበ ወስቴቱ ነውር ወዘአውሰበ አሐተ ብእሲተ ዘንቁሕ በሕሊናሁ ወእቱ ጠቢብ ወመናዝዝ ወመፍቀሬ ነግድ መምህር ዘኢያበዝኅ ሰትየ ወይን ወዘኢያፈጥን እዴሁ ለዘቢጥ /ፍት. መን. አን.5፤ 1ጢሞ. 3፡1-3፤ ጢት. ዘ፩/ ።

ሐ/ ኤጲስ ቆጶስ በጠባዩ ትሑት÷ የማይጣላ÷ ትዕግሥተኛ ሰውን የሚያስታርቅ ገንዘብ የማይወድ ለሰው የሚያዝንና የሚራራ ቤተሰቡን ሠርቶ ቀጥቶ የሚያኖር ልጆቹን ሠርቶ ቀጥቶ የሚያሳድግ መክሮ አስተምሮ በንጽሕና እንዲኖሩ የሚያደርጋቸው÷ ሰካራምና ቁጡ ያልሆነ ከቂም በቀል ከዐመፃ የተለየ ሐዲስ አማኒ ያልሆነ እንዲሆን ታዟል /1ጢሞ. 3፡3-7 ፤ ፍት. ነገ. አን. 5/ ።

መ/ ኤጲስ ቆጶስ ከ50 ዓመት በታች እንዳይሾም ተከልክሏል ። "ወዘኢኮነ ሕይወቱ ሀፁፀ እም ፶ ዓመት" /ፍት. ነገ. 5 ፤ ድስቅ ፬/ ።

ሠ/ ኤጲስ ቆጶስ ብሉይ ሐዲስ የተማረ እንዲሆን ታዟል ።

ረ/ ኤጲስ ቆጶሱን የሚመርጡት 30 ዘመን የሆናቸው ናቸው /ፍት. ነገ. አን. 5 ፤ ጠሰ. 28/ ።

ሰ/ ኤጲስ ቆጶስ የሚሾመው በሚሾምበት አገር ምእመናን ምርጫና በርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ፈቃድ ነው /ፍት. ነገ. አን. 5/ "ለይሠየም ኤጲስ ቆጶስ በኀርየተ ኵሎሙ ሕዝበ ዘአሁ በሥምረተ መንፈስ ቅዱስ" /ፍት. ነገ. አን 5 ድስቅ 36/ "እመቦ ብእሲ ዘአምጽእዎ ከመይስየም ኤጲስ ቆጶስ ወይኩን ዝንቱ በሥምረተ ሰብአብሔሩ ኵሎሙ ወይኩን ዘንቱ ጳጳስ አው ሊቀጳጳሳት ዘይሰየም ..." /ፍት. ነገ. አን. 5 ፤ ረስጣ (አብጥሊስ) 2/።

ሸ/ ካህናትና ሕዝቡ እንዲሾምላቸው ኤጲስ ቆጶስ የሚሆነውን ቆሞስ መርጠው ሲያቀርቡ ስለደግነቱና ትሩፋቱ÷ ስለንጽሕናውና ከነውር የራቀ ስለመሆኑ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳቱ ሦስት ጊዜ እየመላለሰ ማረጋገጫ ይጠይቃቸዋል ። ሕዝቡም አረጋግጠው የሚገባው ነው ብለው ሦስት ጊዜ መልስ ይሰጣሉ ። በሦስተኛው ሕዝቡ መልስ ሲሰጡ እጃቸውን እንሥተው ይገባዋል እያሉ ያጨበጭባሉ ። ወይም አመልጥነው አማን በአማን እያሉ ያሸበሽባሉ ። ከጨበጨቡ በኋላ ተቃውሞ ቢነሣ ያስታርቁታል እንጂ ተቀባይነት የለውም/ፍት. ነገ. አን. 5 ፤ ረስጠብ 52/ ።

ቀ/ በሹመቱ ጊዜ ሦስት ወይም ሁለት ኤጲስ ቆጶሳት ከርእሰ ሊቃነ ጳጳሳቱ ጋር አብረው ይሾማሉ እንብሮተ እድ ያደርጋሉ ። "... ወየሃልዉ ለሢመተ ኤጲስ ቆጶሳት ክልኤቱ አው ሠለስቱ እስመ ዝንቱ ውእቱ ዘ ዌስክ ሞገስ /ፍት. ነገ. አን. 5 ፤ ረስጣ (አብጥሊስ) 2/ ።

"ወየሃልዉ ከመ ይሢምዎ ፪ቱ ኤጲስ ቆጶሳት አው፫ቱ" /ፍት. ነገ. አን. 5፤ ረስጣ 3 (ቀሌ)4/።

በ/ ጋኔን ያደረበት ሰው ኤጲስ ቆጶስነት አይሾምም ። "ኢይደሉ ከመ ይኩን ኤጲስ ቆጶስ ዘጋኔን /3 ቀሌ 2/ ።

ተ/ ዕውር ደንቆሮ ሰነፍ ዝንጉ ኤጲስ ቆጶስ አይሆንም ። "ወኢይደሉ ከመ ይኩን ዕውር ወኢጽሙም ወኢዝንጉዕ" /3ቀሌ 52 ፤ ፍት. መን. 5/ ።

ቸ/ ደግነቱ ያልታወቀ÷ በራሱ ፈቃድ ዐባለዘሩን የሰለበ÷ ቀድሞ ሳያምን ኖሮ በኋላ የተጠመቀ÷ ኃጢአተኛ ሁኖ በኋላ ንስሐ የገባ÷ ኤጲስ ቆጶስነት አይሾምም /ፍት. መን 5 ፤ ረስጠ፳ /3 ቀሌ. 75 ።

ኀ/ ኤጲስ ቆጶስ ከአንድ ኤጲስ ቆጶስ አይሾምም ።

"ወኢይደሉ ከመ ይሠየም ለከሙ እምአሐዱ ኤጲስ ቆጶስ እስመ ስምዐ ክልዔቱ አውሠለስቱ ይከውን ቀዋሚ ወለእመ ኮነ ውእቱ ኤጲስ ቆጶስ አሐዱ ዘእንበረ እዴሁ ላእሌሁ ይትፈለጥ" /ፍት. መን. አን. 5 ፤ ረስባ 58 ድስቅ 34/ ።

ነ/ አንድ ዓይንና እንከባ ኤጲስ ቆጶስነት ከመሾም አያከለክልም ። ይኸውም አንካሳው ዞሮ የሚያጥን፥ ዓውድ የማይጥል፥ አንድ ዓይናው ቀለም የማይጥል፥ ፍታቴ የሚያደላድል ከሆነ ነው ።

"ወኢይትከላዕ ከመ ይኩን ኤጲስ ቆጶስ ነቋር ተ ወኢሐንካስ፥ ለእመ ኮነ ይሤኒ ዝግብር" /ፍት መን 5 ፤ ረስጠጅ (3 ቀሌ) አንቀጽ 72/ ።

ኘ/ ኤጲስ ቆጶስ የሚሾመው እሑድ ቀን ነው፥ ተሿሚውን በሚገባው ወንበር ያስቀምጡታል ። "ወይሠየም ኤጲስ ቆጶስ በዕለተ እሑድ" /ፍት መን. 5 ድስቅ. 37/ ።

አ/ ኤጲስ ቆጶስ ሲሾም ካህናቱም ሕዝቡም በሙሉ ተገኝተው እየመሰከሩለት ነው የሚሾመው ። "ወኵሎሙ ሰብእ ይንበሩ በእንተ ተሰይሞቱ ሕዝብ ኒ ወካህናት እንዘ ስምዐ ይከውኑ ሎቱ" /ፍት. መን. 5/ ።

ከ/ በአንብሮተ እድ ኤጲስ ቆጶሱን ሲሾሙ የተሰበሰቡ ኤጲስ ቆጶሳት እጃቸውን ይታጠባሉ ። ከታጠቡ በኋላ በአንብሮተ እድ ይሾሙታል ።

"ወኤጲስ ቆጶሳትኒ እለ መጽኡ ከመ ያንብሩ እደዊሆሙ ዲቤሁ ይትሐፀቡ እደዊሆሙ ወእምዝ ይሢምዎ" /ፍት. መን. አን. 5/ ።

ኸ/ ኤጲስ ቆጶሳት በአንብሮተ እድ ሲሾሙት ሕዝቡ በፍርሃት ፀጥ ብለው ይቆማሉ ። "ወሕዝብ ቀዊሞሙ በአርምሞ ወበፍርሃት ያንሥኡ ወያንብሩ ኤጲስ ቆጶሳት እደዊሆሙ ዲቤሁ" /ፍት. መን. 5/ ።

ወ/ ኤጲስ ቆጶሳት በአንብሮተ እድ ሲሾሙ "ንሁን ናንብር እደዊነ ዲበ ዝንቱ ገብር ኅሩይ ዘእግዚአብሔር በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ" እያሉ የቡራኬ ቃላት እየተናገሩ ነው /ፍት. መን. አን. 5/ ።

ዐ/ ኤጲስ ቆጶሳቱ የአንብሮተ እዱን ጸሎት ቡራኬ ከፈጸሙ በኋላ ለተሿሚው መስቀል ይሰጡታል /ፍት. መን. 5/ ።

ዘ/ ኤጲስ ቆጶሳቱ በአንብሮተ እድ በሚሾሙበት ጊዜ በመጀመሪያ የተሾመው ኤጲስ ቆጶስ ከአለ ከርእሰ ሊቃነ ጳጳሳቱ ቀጥሎ በቀድሚያ አንብሮተ እድ ያደርጋል ÷ እጁን ከእጅ ላይ ይጭናል ።

"ወእምድኅረ ዝንቱ ያንብር ኤጲስ ቆጶስ ቀዳማዊ እምኔሆሙ እዴሁ ዲቤሁ" /ፍት. መን. አን. 5/።

ዠ/ ከዚህ በኋላ ጸሎተ ሢመቱን ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳቱ ይጸልያል ÷ ሕዝቡ "አሜን" ይላሉ /ፍት. መን. አን. 5/ ።

የ/ ጸሎተ ሢመቱም ሲያበቃ ኤጲስ ቆጶሳቱ ተሹዋሚውን እጅ ይነሡታል ፤ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳቱ በአንብሮተ እድ በንፍሐት መንፈስ ቅዱስን ያሳድርበታል ። በዚህ ጊዜ ካህናቱና ሕዝቡ "ይደልዎ÷ ይደልዎ÷ ይደልዎ" ይላሉ ። ይህንንም ምስክርነት በከፍተኛ ድምፅ እያሰሙ ካህናቱና ሕዝቡ ተሹዋሚውን እጅ ይነሡታል ። "ወይኩን ፍቁረ ለኩሉ ወለኩሉ ግብር ሠናይ ዘሀሎ ላእለ ሰብእ ለይርባሃ ለነፍሱ እስመ ኖላዊ ለእመ ርሕቀ እምዓመፃ ይስሕቦሙ ለአርዳኢሁ... በከመ ይቤ ሆሴዕ ነቢይ እስመ በከመ ይከውን ካህን ከማሁ ካዕበ ሕዝብኒ" /ፍት. ነገ. አን. 5 ፤ ድስቅ 8 ፤ ሆሴዕ 4፡9/።

ፐ/ ኤጲስ ቆጶስ ከተሾመ በኋላ ቤተ ክርስቲያንን ዘወትር ያገለግላል ፤ በመዓልትም በሌሊትም ስለራሱና ስለሕዝቡ÷ ስለ ሀገሩና ስለዓለሙ ይጸልይ ዘንድ ታዟል ፤ በቤተ ክርስቲያን ብቻውን ይኖራል ማለት ቤቱን ከቤተ ክርስቲያን አጠገብ ያደርጋል ። ካስፈለገው በጸሎተ ማኅበር የሚረዱት አንድ ሰው÷ ሁለት ሰው በቤቱ ለማኖር ይችላል ።

"ወለእመ ኮነ ሎቱ ዘያሠምሮ ለነቢር ምስሌሁ እመ አኮ አሐዱ አው ክልዔቱ ወውእቶሙ አሐቲ ነፍስ ምስሌሁ ይግበር በዘይትራድእዎ በእንተ ዘይደሉ" /ፍት. ነገ. አን. 5/ ።

ቈ/ ኤጲስ ቆጶስ ቀሳውስትን ይባርካል ፤ እሱ ግን በቀሳውስት አይባረክም "ኤጲስ ቆጶስ ይባርክ ወኢይባርኩ ኪያሁ" /ፍት. ነገ. 5 ረስጣ (ቀሌ) 21/ ።

ኖ/ ኤጲስ ቆጶስ ከቀሳውስት እስከ ዓፃዌ ኖኅት ያለውን ሹመት ይሾማል ፤ ነገር ግን ሳይመረምር፥ ሳይፈትን ማንንም ክህነት እንዳይሾም ተከልክሏል ። "ወኢታፍጥን አንብሮ እዴከ ላእለ አሐዱሂ ወኢትሳተፍ በዝንቱ ኃጢአተ ካልዕከ" /1ጢሞ. 5፡22 ፤ ፍት. ነገ. አን. 5 ክፍል 4/ ።

ኰ/ ከኤጲስ ቆጶስ በስተቀር መሻር የሚገባውን ካህን ይሽራል /ፍት. ነገ. አን. 5 ክፍል 4/ እግዚአብሔር እንደሾመው ኖላዊነት በእሱ ብቻ ሳይሆን በሕዝቡም ኃጢአት ስለሚጠየቅ ተግቶ ማስተማርና ሕዝቡን ከኃጢአት መጠበቅ እንዳለበት ታዟል ።

"አንተሰ ያርከ ያረ ክቡደ ጽሑፍ ከመ እግዚአብሔር ይቤሎ ለሙሴ አንተ ወአሮን ትፀውሩ አበሳሆሙ ለሕዝብ... ወሶበ መጽአ ኀቤከ ዘሀለወ ቦቱ ዓቢይ አበሳ ኢትትሀየይ ኪያሁ ይቤ ሕዝቅኤል ነቢይ በእንተ ኤጲስ ቆጶስ ዘይትሄየይ እንበይነ ሕዝቡ አሌ ሎሙ ለኖሎተ እሥራኤል እለ ኀደጉ አባግኢሆሙ ዘይርዕዩ ለለ አሐዱ አኮኑ አንትሙ ኖሎት ዘትርዕዩ አባግዐ ወአንትሙ ለሀሊብ ትሰትይዎ ወለፀምር ዘትለብስዎ ወለመግዝዕኒ ሰቡሕ ዘትጠብህዎ ወአባግዕየሰ ኢትርዕዩ ..." /ሕዝ. 34፡1-19 ፤ ፍት . ነገ. አን. 5/ ።

ጐ/ ኤጲስ ቆጶስ ስሙ በጸሎት ላይ ይጠራል ፤ በቅዳሴም ይነሣል /ፍት. ነገ. 5 ክፍል 4/

ኗ/ ኤጲስ ቆጶስ ሥጋውን ደሙን ከኤጲስ ቆጶሳት እንጂ ከቀሳውስት አይቀበልም /ፍት. ነገ. 5 ክፍል 4/

ሟ/ በካህናት መካከል እኔ በላይ፥ እኔ በላይ ልቁም፥ ልቀመጥ በማለት ጠብ ክርክር እንዳይሆን፥ ካህናትም በማዕረግ ከሕዝቡ ጋር አንድ እንዳይሆኑ፥ ሊቃነ ካህናት ከተራ ካህናት ጋር እኩል እንዳይሆኑ የካህናቱን ማዕረግና መቆሚያቸውን ማወቅና ጽፎ መያዝ እንደሚገባው ታዟል "ወይደልዎ ከመይጽሐፍ ወያእምር ኵሎ ማዕርጋተ ካህናት ወሥርዓታቲሆሙ ከመ ኢይኩን ማእከሌሆሙ ጋዕዝ በዝንቱ ግብር ወከመ ኢይደመሩ ሰብአ ቤተ ክርስቲያን እንተ ሐዋርያት ምስለ ሕዝባውያን ወከመ ኢይኩኑ ምስለ ሊቃነ ካህናት እንተ ሐዋርያት ምስለ ሕዝባውያን በመዓርግ በአምሳሊሆሙ /የኒቅያ ሲኖዶስ አን 67/ ።

ሯ/ ኢጲስ ቆጶስ የተሾመበትን ሀገር ከተማና ገጠር ትቶ በሌላ ሀገር እንዲቀመጥ አልተፈቀደም ። "ወኢይደልዎ ለኢጲስ ቆጶስ ከመይኅድግ መንበሮ ወሀገሮ ወይሑር ኀበ ካልዕ ሀገር" /2ቀሌ 11/ ።

ሷ/ ኢጲስ ቆጶስ የተሾመበትን ሀገር ለቆ ወደ ሌላ ሀገር መዛወር እንደሌለበት ባል ሚስቱን ፈትቶ ሌላ ማግባት የማይገባውን ያህል አይገባውም ተብሎ ታዟል "ወኢይሑር ኤጲስ ቆጶስ ኀበ ካልዕ ሀገር እምነ ሀገሩ ዘከነ ላእሌሁ ወተሠይመ ኤጲስ ቆጶስ በእንተ ራሕበብሔር ወናዕስ ዘአሃወ ውህደተ ሰብእ ወበረከታቲሃ ወዝንቱሰ ይትሚሰል እምሳለ እለ አውሰቡ ብእሲተ እምነ ሕዝባውያን
ነመ ተአቅፈ ብእሲ በብእሲቱ ዘእንበለ
ከንያተ ዝሙት ለእመ ፈቀደ ወልጠታ
ሄኒ እምኔሃ ወእቱ መዓብስ ፈድፋደ ወከማሁ

ኢጲስ ቆጶሳትኒ ወካህናት እምሳለ የሐ[illegible] ፈድፋደ ዘይኄይስ እምሀገሮሙ/ ጉባኤ ኒቅያ 77/ ።

ሿ/ ኤጲስ ቆጶስ ቢያጠፋ ያላመኑ ሰዎች ምስክርነት ወይም የአንድ ኤጲስ ቆጶስ ምስክርነት አይሰማበትም "ኢይትወከፉ ስምዐ ሐራጥቃ ዘውእቶሙ አላውያን ላዕለ ኢጲስ ቆጶስ ወኢይትወከፉ ላዕሌሁ ስምዐ አሐዱ ኤጲስ ቆጶስ" /3ቀሌ. አን. 70፤ 2ቀሌ. 12/።

## ጉባኤ ኤጲስ ቆጶሳት /ሲኖዶስ/

ሀ/ ኤጲስ ቆጶሳት በዓመት ሁለት ጊዜ ይሰበሰባሉ ። "ወይኩን ጉባኤ ኤጲስ ቆጶሳት ክልኤተ ጊዜ በበዓመት" /ፍት. መን. አን. 5 ክፍል 5 ፡ ረስጠብ 27፤ ረስጠጅ 28፤ ጸክ 28/ ።

ለ/ የመጀመሪያው ጉባኤ በበዓለ ሃ በ4ኛው ሱባኤ በአራተኛው ቀን ይደረጋል ፤ ይኸውም ርክበ ካህናት በሚውልበት ዕለት ማለት ነው ።

ሁለተኛው ጉባኤ ጥቅምት በባተ በ12ኛው ቀን ይደረጋል ፤ ይህም ዕለት ዕለተ ዕረፍቱ ለማቴዎስ ወንጌላዊ ነው ።

"ወጊዜ ቀዳሚት ጉባኤ በራብዕ ሱባኤ እምሃምሳ÷ ወዳግሚትኒ አመ ፲ወ፪ ለጥቅምት /ፍት. መን. 5 ክፍል 5/ ።

"ይትጋብኡ ኤጲስ ቆጶሳት ዘኩሉ መካናት ኀበ ጳጳሶሙ አው ኀበ ሊቀ ጳጳሳቲሆሙ ክልዔተ ጊዜ በኩሉ ዓመታት" /ፍት. መን. አን. 5፤ ኒቅያ 9 ፤ 45/ ።

ሐ/ በጉባኤው መካከል አንድ መንበር ተደርጎ በላዩ ላይ ወንጌል ይቀመጣል ፤ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳቱ በፊት ለፊት ይቀመጣል ፤ በር ይዘጋና ኤጲስ ቆጶሳት ተነሥተው የማኅበር ጸሎት ያደርጋሉ ፤ ጸሎቱ ሲያልቅ ይቀመጣሉ÷ ከዚያ በኋላ ስለሃይማኖት መጽናት÷ ስለ በጎ ምግባር መስፋፋት÷ ስለ ሥርዓት ቤተ ክርስቲያን መቃናት÷ በጠቅላላው ስለ መንፈሳዊ ሕግና ፍትሕ ተነጋግረው ውሳኔ ይሰጣሉ ።

"ወያንብሩ ማዕከለ ምርፋቆሙ አሐደ መንበረ ወያንብርዎ ዲቤሁ ለወንጌል ቅዱስ ወይነበር ሊቀ ጳጳሳት በቅድሜሆሙ ወይዕፁ አናቅፀ ወይትነሥኡ ኅቡረ ወይጸልዩ ወይግብኡ ኀበ ምርፋቆሙ ወይሕትቱ በእንተ ግብር ዘተጋብኡ በእንቲአሁ በኅቡዕ" /ፍት. መን. 5 ክፍል 5/

## ሐ/ የሢመተ ቀሳውስት ሥርዓት

### 1/ ለቅስና ሹመት የሚያበቁ ሁኔታዎች

ሀ/ ለቅስና የሚመረጥ ዲያቆን ነውርና ነቀፋ የሌለበት÷ አንዲት ድንግል ሴት ያገባ÷ ደኅና ልጆች ያሉት÷ ቂመኛ ያልሆነ÷ አብዝቶ የማይጠጣ÷ እጁን ለመማታት እንደበቱን ለመገዘት የማያፈጥን÷ ገንዘብ የማይወድ÷ እንግዳ የሚቀበል÷ በጎ ሥራን የሚያፈቅር÷ ከኃጢአት የነፃ÷ ደግና ቸር የሆነ ሰውነቱን ከፍትወት የገታ ወንጌልን በማስተማር ምእመናንን የሚረዳ÷ እውነተኛ ትምህርት በማስተማር ሰውን ማጽናናት የሚቻለው÷ ክደው ሊያስክዱ የሚተናኮሉትን የሚከራከራቸው መሆን እንዳለበት ተሠርቷል /ፍት. መን. አን. 6 ክፍል 1 ዘሌ. 21፡7-16/።

ለ/ ሠላሳ ዓመት ያልሞላው እንዳይሾም ተከልክሏል ።

"ኢይሠየም ቀሲስ ዘእንበለ በ፴ ዓመት" /ፍት. መን. 6 ቀጠግ. 11/

ሐ/ ብሉያትን ሐዲሳትን ያልተማረ÷ ይልቁኑም አራቱን ወንጌል ያላወቀ ቅስና እንዳይሾም ተከልክሏል ።

"ወኢይኩን አሐዱሂ ቀሲስ ዘኢየአምር ነገረ መጻሕፍት አምላካውያት ሠናያት" /ፍት. መን አን. 6 በስ. 89/

መ/ ለቅስና መብቃቱ ያልተመሰከረለት ቅስና አይሾምም ።

"ወኢይኩን አሐዱሂ ቀሲስ ዘኢተንአደ በሰምዐ ሐምስቱ ዕደው" /ፍት. መን. አንቀጽ 6 ፤ በስ. 47/

## 2/ ሢመተ ቅስና

ሀ/ ኢ.ጳ.ስ ቆጶስ በአንብሮተ እድ ይሾመዋል ፡ ቀሳውስት ቆመው ይዳስሱታል፡ ይጸልዩለታል። ቄስ÷ ዲያቆን÷ ንፍቀ ዲያቆንና ከዚያ በታች ያሉት የሚሾሙት በኢ.ጳ.ስ ቆጶስ ብቻ ነው÷ ኢ.ጳ.ስ ቆጶሱ እነዚህን ሲሾም የማዕረጋቸውንና የሥርዓተ ክህነታቸውን ደረጃ ጠብቆ በሕዝብ ፊት ጸሎተ ሲመቱን አድርሶ ይሾማቸዋል ።

"ወለእመ ፈቀደ ኢ.ጳ.ስ ቆጶስ ከመይሢም ቀሲስ ያንብር እዴሁ ላእለ ርእሱ ወቀሳውስትኒ ኵሎሙ ይገሥሥዎ ቀዊሞሙ ወይጸልዩ ላእሌሁ /ፍት. መን. አን. 6 ክፍል 2 ረስጣ 22፡54/ ።

ለ/ ኢ.ጳ.ስ ቆጶስ ሳይፈቅድ ቄስና ዲያቆን አይሾምም ።

"ወኢይሠየም ቀሲስ አው ዲያቆን ዘእንበለ በምክረ ኤጲስ ቆጶስ ዘውእቶሙ ታሕተ ሥልጣኑ ወይሢም ኤጲስ ቆጶስ ባሕቲቱ እስመ ሳልሣይ ማእርጊሁ" /ፍት. መን. አን. 6 ክፍል 2 በስ. 10 ረስጣ 2/።

## 3/ የቀሳውስት ተግባርና ሥልጣን

ሀ/ ቄስ መምህር ነው ፤ መምህርም እንደመሆኑ የቀናች ሃይማኖትን ያስተምራል ። "እስመ ቀሲስ በአምሳለ መምህር ። ወይኩኑ ቀሳውስት በኀቤክሙ መምህራነ ለአእምሮተ እግዚአብሔር /ፍት. መን. አን. 6 ድስቅ 27/ ።

ለ/ ቄስ ሥራው ማስተማር÷ ማጥመቅ ቀድሶ ማቁረብ መባረክ ማሠርና መፍታት መናዘዝ ነው /ፍት. መን. አን. 6 ክፍል 3/ ።

ሐ/ ቄስ በአንብሮተ እድ ሕዝቡን ይባርካል ።

"ወይባርክ ወኢይትባረክ እምዘ ውእቱ ይንእስ" /ፍት. መን. አን. 6 ረስጣ 58/

መ/ ቄስ ሥልጣነ ክህነት አይሾምም ፤ አይሽርም። /ፍት. መን. 6 ክፍል 3/

## 4/ ትእዛዘ ቀሳውስት

ሀ/ ቄስ ምእመናንን መጠበቅና ሲታመሙ መጠየቅ፥ ፡ በትምህርት ማጽናት እንደሚገባው ታዝዋል ። እውነተኛ ፍርድ መፍረድ ይገባዋል /ፍት. መን. 6 ክፍል 4/ ።

ለ/ በመሠዊያው ቀኝ የሚቆሙ ቀሳውስት ካህናቱን ያስተናብራሉ ፤ ሥጋ ወደሙ የሚቀበሉትን በየተራቸው እንዲቀበሉ ይቈጣጠራሉ ። በግራ የሚቆሙ ቀሳውስት ሕዝቡን ያስተናብራሉ ። "ወቀሳውስት እለ ውስተ የማን ያስተሐምሙ ለረድኤት በውስተ ምሥዋዕ ከመ ያክብርዎ ለዘይደልዎ ክብር ወይመንንዎ ለዘይደልዎ ምናኔ ወቀሳውስትሰ እለ ውስተ ጸጋም ያስተሐምሙ በእንተ ጉባኤ ከመ ይኩኑ ኅዱዓነ" /ፍት. መን. አን. 6 ክፍል 4/ ።

ሐ/ ቀሳውስት ሐዋርያት ከሠሩት ሥርዓት ውጭ ትእዛዝ በማክበድ ሕዝቡን እንዳያስጨንቁ ታዝዋል ። "ወኢይወስክ አሐዱ እምቀሳውስት ምንተኒ ክበደ ውጹአ እምቀኖና አበዊነ ሐዋርያት /ፍት. መን. 6 በስ 51/ ።

መ/ ቄስ ታቦ በሚመረመርበት፥ በሚታከምበት ጊዜ ከአልሆነ በስተቀር በማንም ጊዜ ፈጽሞ ዕርቃኑን ሊጥልና ሊጋለጥ አይገባውም ።

"ወኢይትዓረቅ ቀሲስ ግሙራ ቅድመ መኑሂ እምስብእ ዘእንበለ በጊዜ ዕጸባ" /ፍት. መን. አን. 6 ክፍል 4 በስ 53/ ።

ሠ/ ቀሳውስት ከኤጲስ ቆጶሱ ዘንድ በየዓመቱ 3 ጊዜ እንዲሰበሰቡ ታዝዋል ።

"ወይትጋብኡ ቀሳውስት ኀበ ኤጲስ ቆጶሳት ሀሙ ሠለስተ ጊዜያተ በበዓመት /ፍት. መን. አን. 6 ክፍል 4 ኒቅያ 59/ ።

ረ/ ካህናት የራስ ጠጉራቸውን ማሳደግና ማጎፈር አይገባቸውም ።

## 5/ ቀሳውስት ከሹመት የሚሻሩበት ሥርዓት

ሀ/ በሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን ሊጠብቀው የታዘዘውን የማይጠብቅ፥ እንዳይሠራው የተከለከለውን

የሚሠራ በሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን ሕዝቡን የማያስተምርና የማይመራ ቄስ ቢኖር ከክህነቱ ይሻራል /ፍት. መ'ን. አን. 6 ክፍል 5/ ።

ለ/ ሁለት ጊዜ የተሾመ ሁለት ጊዜ ያገባ፥ ወይም ሁለት ሚስት ያለው ሕዝቡን የማያስተምር፥ የተቸገሩትን ካህናት የማይረዳ፥ ጉቦ ሰጥቶ የተሾመ፥ የኃጢአተኛውን ንስሐ የማይቀበል፥ በሐሰት የሚመሰክር፥ ሰውን የሚያጣላ ፥ የሚኮራ፥ የክፋትን ሥራ የሚሠራ፥ የሚሰክር፥ ከከብ የሚቆጥር፥ አራጣ /ወለድ/ የሚቀበል፥ በሐሰት የሚምል፥ የጠንቋዮችን ነገር እውነት ነው ብሎ የሚቀበል፥ ከሴሰኛ ሴት የደረሰ፥ ሥር የማሰ፥ ቅጠል የበጠሰ፥ ሰውን የሚማታ፥ ከመናፍቃን የተጠመቀ፥ የሰረቀ፥ የመናፍቃንን ቁርባን የተቀበለ፥ አብሮአቸው የጸለየ፥ ዐባለ ዘሩን የሰለበ፥ ሲሰስን፥ በሐሰት ሲምል የተገኘ፥ በገበያ መካከል የሚበላ፥ በመሸታ ቤት ገብቶ የሚጠጣ፥ የበከተውንና የአውሬውን ትራፊ የሚበላ ፥ ከአይሁድ ምኩራብ፥ ከዐላውያን ቤተ ክርስቲያን የሚገባ፥ የአይሁድን ጾም የሚጾም፥ በዓላቸውን የሚያከብር፥ የበዓላቸውን እጅ መንሻ የሚቀበል፥ ሃይማኖታቸውን ወደለወጡ ሰዎች ቤተ ክርስቲያን እጅ መንሻ የሚወስድ፥ ከተወገዘ ሰው ጋር የተነጋገረ፥ አብሮት የጸለየ፥ የኤጲስ ቆጶሱን ደብዳቤ ሳይዝ ሩቅ አገር የሄደ፥ በአገልግሎት ምክንያት ሚስቱን የተለየና የፈታ፥ እመነኩሳለሁ ተባሕትዎ እይዛለሁ ብሎ ሚስቱን የተወ፥ ያሰናበተ ካህን ከሹመቱ ይሻራል /ፍት. ነገ. አን. 6 ክፍ. 5 ፤ 2ቀሌ 3 ፤ 3ቀሌ 5/ ።

ሐ/ ቄስም ሆነ ዲያቆን ከሹመቱ በኃጢአት ከተሻረ በኋላ ደፍሮ ለአገልግሎት ቢገባ ከቤተ ክርስቲያን ተወግዞ ከምእመናን ይለያል ። እያወቁ በዚህ ድፍረቱ የተባበሩት ሁሉ ከምእመናን ይለያሉ ። /ፍት. ነገ. 6 ፤ ረስጠብ (2ቀሌ) 19 ፤ ጸክ 4/

መ/ ቄስ ወይም ዲያቆን በሀገሩ የተሾመውን ኤጲስ ቆጶስ ንቆ አቃሎ ለብቻው ቤተ ክርስቲያን ከሠራ ኤጲስ ቆጶሱ እስከ ሦስት ጊዜ ጠርቶት ካልመጣ እሱና የመሰሰሉት ከሹመታቸው ይሻራሉ ። /ፍት. መ'ን. 6 ፤ ረስጠብ (2ቀሌ) 22/ ።

ሠ/ ቄስ ያለበትን ቤተ ክርስቲያን ትቶ ወደ ሌላ ቤተ ክርስቲያን ከሄደ÷ እንዲመለስ ተነግሮት ካልተመለሰ ከሹመቱ ይሻራል /ፍት. ነገ. 6 ፤ ረስጠብ (1ቀሌ) 14 ፤ ኒቅያ 4፡4/ ።

ረ/ ቄስ በቁጣ ወይም በማናቸውም ምክንያት ምእመናንን ሥጋ ወይመን ከከለከለ ከሥልጣኑ ይሻራል /ፍት. መን. አን. 6 ክፍል 5 ፤ ኒቅያ 27/ ።

ሰ/ ቀሳውስትና ዲያቆናት በሥጋዊ ነገር ዋስ÷ ተያዥ÷ ምስክር አይሆኑም ይህን ያደረገ ከሹመቱ ይሻራል /ፍት. መን. 6 ክፍል 5 ኒቅያ 28/ ።

መ/ <u>የሢመተ ዲያቆናት ሥርዓት</u>

1/ <u>ለዲቁና ሢመት የሚያበቁ ሁኔታዎች</u>

ሀ/ ዲያቆናት ጭምቶች÷ ትዕግሥተኞች÷ ግብረ ገብነት ያላቸውና የሚታዘዙ÷ ሁለት ቃል የማይናገሩ ማለት አንድ ጊዜ እውነት አንድ ጊዜ ሐሰት የማይናገሩ÷ አብዝተው ወይን የማይጠጡ÷ የማይገባ ትርፍ ገንዘብን መቀበል የማይሹ÷ ንጹሕ በሆነ ልቡና ሃይማኖትን የተረዱ÷ ጋብቻ ያልደገሙ÷ ልጆቻቸውን ቤተ ሰቦቻቸውን ቀጥተው ያሳደጉ መሆን ይገባቸዋል ። በዚህ ሁሉ የተፈተኑና ነውር የሌለባቸው ሆነው ሲገኙ ዲቁና ይሾማሉ /1ጢሞ. 3፡8-12 ፤ ፍት. መን. 7 ክፍል ፤ 1 ፤ ጠት. 4/ ።

ለ/ በሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን መሠረት ለመዓርገ ዲቁና መብቃታቸው ተመስክሮላቸው እንዲሾሙ ታዝዞዋል/ፍት. ነገ. 7 ፤ ረስጣ 17/ ።

ሐ/ ከዚህ ጋር ለሰው የሚራሩ÷ የሚያዝኑ÷ የማያንጐራጉሩ÷ ከቂም በቀል የራቁ÷ ቁጡዎች ባለጌዎች ያልሆኑ÷ የማያዳሉ÷ ለመማርና ለማስተማር የተጉ እንዲሆኑ ታዝዞዋል /ፍት. መን. አን. 6 ክፍል 1/ ።

## 2/ ሢመተ ዲቁና

ሀ/ ዲያቆን በአንብሮተ እድ ይሾማል ። "ሶበ ትሤይሞ ለዲያቆን አንብር እዴከ ላዕሌሁ ወጸሊ" /ፍት. መን. አን. 7 ክፍል 2 ረስጣ 54 ቀጠግ 54/ ።

ለ/ ዲያቆናት ሲሾሙ ቀሳውስትና ዲያቆናት ከኤጲስ ቆጶሱ ጋር ሆነው አብረው ይጸልያሉ ። አንብሮተ እድ የሚያደርግለት ግን ኤጲስ ቆጶሱ ብቻ ነው ።

"ቀሳውስት ኩሎሙ ወዲያቆናትኒ እንዘ ይቀውሙ ይጸልዩ" /ፍት. መን. አን. 7 ክፍል 2 ፤ ረስጣ 54 ቀጠግ 14/ ።

ሐ/ "ዲያቆን 25 ዓመት ሳይሞላው አይሾምም" ይላል ÷ ይሁን እንጂ ብቁ ሆኖ ከተገኘ ከዚህ ዕድሜ በታችም ያለ ቢሆን ይሾማል /ፍት. መን. አን. 7 ክፍል 2 ፤ ቀጠግ 11/ ።

መ/ የዲያቆናቱ ቁጥር በቤተ ክርስቲያኑ ስበካ ስፋትና ጥበት ይወሰናል /ፍት. መን. አን. 7 ፤ ቀጠግ 14 ኒቅያ 67/ ።

## 3/ የዲያቆናት ሕይወትና ሥርዓት

ሀ/ ዲያቆናት እንደ ኤጲስ ቆጶስ ÷ እንደ ቄስ ያለ ነውር ያለ ነቀፋ መኖር አለባቸው ። "ወይኩኑ ካዕበ ዲያቆናት ዘእንበለ ነውር በአምሳለ ኤጲስ ቆጶስ ወይኩኑ ፍጹማን በክህነቶሙ ለቤተ ክርስቲያን በዘይከሉ ገቢረ ዘእንበለ ሐፍረት" /ፍት. መን. አን. 7 ክፍል 3 ድስቅ 37/ ።

ለ/ ዲያቆናት በቦታው ሁሉ በመዓልትም በሌሊትም በጎ ሥራን የሚሠሩ መሆን ይገባቸዋል ። ከኃጢአት ንጹሕ ሆኖ መልካም አገልግሎትን የሚያገለግል ዲያቆን ይረባል ÷ ይጠቅማል ÷ በጎ ዕድል ፈንታን ያገኛል /ፍት. መን. አን. 7 ክፍል 4 ረስጣ 18/ ።

ሐ/ ዲያቆን የእግዚአብሔር አገልጋይ እንደ መሆኑ መጠን ለኤጲስ ቆጶሱና ለቄሱ ይላላካል ። "ወዲያቆንሰ ከመ ዘይትለአክ ለእግዚአብሔር ይትለአክ ለኤጲስ ቆጶስ ወለ ቀሳውስት በኩሉ ግብር /ፍት. መን. አን. 7 በዴ. 5/ ።

መ/ ዲያቆን ሕመሙማንን በመጎብኘት የችግረኞችን ጉዳይ ወደ ቄሱ ወደ ኤጲስ ቆጶሱ በማቅረብ ለችግረኞች ምጽዋት የሚሰጡትን ምእመናንን ሁሉ በማስተባበርና በመላላክ እንዲያገለግል ታዝዞዋል /ፍት. መን. አን. 7 ክፍል 3/ ፡፡

ሠ/ በምሥራቅ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ አብያተ ክርስቲያናት ዲያቆናት ወንጌል ያነብባሉ ፤ በእኛ ቤተ ክርስቲያን ግን አያነብቡም ፡፡

"ወያንብብ ወንጌለ እመሂ ዲያቆን ወእመሂ ቀሲስ" /ዲድስቅልያ 12 ፍት. መን. አን. 7 ክፍል 3/ ፡፡

ረ/ ዲያቆን በጸሎተ ቅዳሴ ጊዜ ሕዝቡ ሥርዓት ይዘው እንዲቆሙና እንዲጸልዩ÷ እንዳይንቀሳቀሱና እንዳይተኙ÷ እንዳይስቁና እንዳይሳለቁ ይቆጣጠራል /ፍት. መን. አን. 12 ድስቅ 12/ ፡፡

ሰ/ ሥጋውን ደሙን በማቀበል ጊዜ ሥጋውን ቄሱ ሲያቀብል ዲያቆን ደሙን ለሕዝቡ ያቀብላል ፡፡ /ፍት. መን. አን. 7 ክፍል 3 ረስጣ 58/ ፡፡

ሸ/ ቆሞሱና ሊቀ ዲያቆናቱ ለኤጲስ ቆጶሱ እንደ ሁለት እጆችና እንደ ሁለት ክንፎች ሆነው ሹመት በሚሰጥበት ጊዜ በቀኙና በግራው ይቆማሉ÷ ወደ ቤተ ክርስቲያን ሲሔድ አብረው ይሔዳሉ÷ ወደ ሌላም ቦታ ሲሔድ አይለዩም ፡፡ ሊቀ ዲያቆናት በቀኙ ይቆማል÷ ሌሎች ግን በግራው ይቆማሉ ፡፡

"ወኮሮአቢስኒ ይኩን በማዕርግ ከመ ክልዔ እደዊሁ ወክልዔ ክነፊሁ ለኤጲስ ቆጶስ ወሶበ የሐውር ኀበ ቤተ ክርስቲያን አው ኀበ ካልዕ ይደሉ ከመይኩን ሊቀ ዲያቆን በየማኑ ወካልዓን በፀጋሙ" /ፍት. መን. አን. 7 ኒቅያ 62/ ፡፡

## 4/ ዲያቆን ከማዕርጉ የሚሻርበት ምክንያት

ሀ/ ጉቦ ሰጥቶ÷ ወይም በጉልበት አስገድዶና አስፈራርቶ ወይም ይህን በመሰለ ሌላ ተንኮል የተሾመ÷ ወይም ሁለት ጊዜ የተሾመ ፡፡

ለ/ ሁለት ሴት ያገባ÷ ወይም በተሾመ ጊዜ ከሴት ርቄ ንጽሕ ጠብቄ እኖራለሁ ብሎ ተሥሎ ከተሾመ በኋላ ስዕለቱን አፍርሶ÷ ሚስት ያገባ÷

ወይም ከዘማዊት ሴት የደረሰ÷ ወይም ተደብቆ ተክሊል ያደረሰ÷ ወይም እመንኩሳለሁ ብሎ ሚስቱን የፈታ ።

ሐ/ ዘወትር የሚሰክር÷ በክፉ ሥራ ጸንቶ የሚኖር÷ በሐሰት የሚመሰክር ።

መ/ አራጣ የሚቀበል÷ ነጋዴ የሆነ

ሠ/ ባልንጀራውን የሚያማ

ረ/ በሰው የሚታበይ÷ ኃይሉን የሚያሳይ÷ ሰውን የሚመታ÷ ኤጲስ ቆጶስ ሳይፈቅድለት የመነኮሰ÷ ኢጲስ ቆጶሱን የናቀና ያቃለለ÷ ኢጲስ ቆጶሱ ጠርቶት አልመጣም ብሎ የቀረ÷ ከደሟ ያልነጻችውን ሴት ወደ ቤተ ክርስቲያን ያስገባ÷ ሥጋውን ደሙን ያሰጠ÷ ከተሻረ በኋላ የክህነት ሥራ የሚሠራ÷ ለብቻው ሌላ ቤተ ክርስቲያን የሠራ ።

ሰ/ ቤተ ክርስቲያን ትቶ ከሔደ በኋላ የተመለሰ÷ ከመናፍቃን የተጠመቀ÷ ቁርባናቸውን የተቀበለ÷ ከመናፍቃን ጋር የጸለየ÷ ቤተ ክርስቲያኑን ትቶ ወደ ሌላ ቤተ ክርስቲያን የሔደ÷ ወታደር የሆነ ከዲቁናው መዓርግ ይሻራል /ፍት. መን. አን. 7 ፤ ክፍል 5/ ።

ሠ/ <u>የንፍቀ ዲያቆናት ሢመት ሥርዓት</u>

1/ <u>ለንፍቀ ዲቁና ሢመት የሚያበቁ ሁኔታዎች</u>

ሀ/ ነገር የማያበዛ÷ የማይሰክር÷ ዋዛ ፈዛዛ የማይናገር÷ በጎ አኗኗር ያለው÷ በጎ ነገርን የሚወድ÷ ታዛዥ የሆነ ።

ለ/ የሃይማኖት ትምህርት ወደሚሰጥበት ጉባኤ የሚሔድ ።

ሐ/ ከሴት ርቆ ንጽሕ ጠብቆ ለመኖር የተመሰከረለት ንፍቀ ዲቁና ይሾማል /ፍት. መን. አን. 8 ፤ ረስጣ 15/ ።

### 2/ ሥርዓተ ሢመተ ንፍቀ ዲያቆናት

ሀ/ ንፍቀ ዲያቆን ማስት ያላገባ ከሆነ ከሴት ርቆ ንጽሕ ጠብቆ እንደኖረ ከአልተመሰከረለት አይሾምም /ፍት. መን. አን. 8/ ።

ለ/ ኤጲስ ቆጶስ ንፍቀ ዲያቆኑን ሲሾም አንብሮተ እድ አያደርግም ፤ በቃል ብቻ ንፍቀ ዲያቆን ብሎ ይሾመዋል /ፍት. መን. አን. 8 ክፍል 2 ፤ ረስጣ 27/ ።

### 3/ የንፍቀ ዲያቆናት ሥራ

ሀ/ ንፍቀ ዲያቆናት ዲያቆናትን ይረዳሉ "ንፍቀ ዲያቆናት ከመ እንተ ረዳእያን" /ፍት. መን. አን. 8 ክፍል 3/ ።

ለ/ ንፍቀ ዲያቆናት በዲያቆናት ቦታ ገብተው በዲቁና መዓርግ ማገልገል፥ ንዋየ ቅድሳት መንካት፥ የዲያቆናትን ልብሰ ተክህኖ መልበስ አይችሉም ። /ፍት. መን. አን. 8 ጾክ. 45፤ 46፤ 47፤ 67፤ 21፤ 22፤ 23፤ 43/ ።

ሐ/ ንፍቀ ዲያቆን በመቅደሱ በር ከውጭ ይቆማል ፤ ከዚያ አይለይም /ፍት. መን. አን. 8 ክፍል 3/ ።

መ/ ንፍቀ ዲያቆን ደሙን አያቀብልም/ፍት. መን. አን. 8 ክፍል 3 ጾክ. 39/ ።

### 4/ ንፍቀ ዲያቆን የሚሻርበት ምክንያት

ንፍቀ ዲያቆን ከሰረቀ አንድ ዓመት ከሹመቱና ከሥራው ይታገዳል ። ከዓመት በኋላ ወደ ሥራው ይመለሳል ወደ ዲቁና ማዕርግ አይደርስም ፤ እስከ ዕለተ ሞቱ በንፍቀ ዲቁና ማዕርግ ይኖራል /ፍት. መን. አን. 8 ክፍል 4 በስ. 48/ ።

## ረ/ የአናጉንስጢስ ሢመት ሥርዓት

### 1/ ለአናጉንስጢስ ሢመት የሚያበቃ ሁኔታ

አናጉንስጢስ ማለት አንባቢ ማለት ነው ። በችሎታው በበጎ ጠባዩ የታወቀ፥ ነገር የማያበዛ፥ የማይሰክር፥ ዋዛ ፈዛዛ የማይናገር፥ በጎ አኗኗር ያለው፥ በጎ ነገርን የሚወድ፥ የሃይማኖት ትምህርት

ወደሚሰጥበት ጉባኤ ለመሔድ የሚፋጠን÷ ታዛዥ÷ የሚያነብበውን ለመሥራት የሚተጋ÷ የሚያነብበውን ኃይለ ቃል የሚያውቅ አናጉንስጢስነት ይሾማል ። /ፍት. መን. አን. 8 ክፍል 1 ፤ ረስጣ 15/ ።

## 2/ ሥርዓተ ሢመተ አናጉንስጢስ

ሀ/ አናጉንስጢስ በሚሾምበት ጊዜ አስቀድሞ ኤጲስ ቆጶሱ አንብብ ብሎ ወንጌል ይሰጠዋል /ፍት. መን. አን. 8 ክፍል 3 ፤ ረስጣ 20/ ።

ለ/ ኤጲስ ቆጶስ አናጉንስጢስን ሲሾም አንብሮተ እድ አያደርግም በቃል ብቻ አናጉንስጢስ ብሎ ይሾመዋል /ፍት. መን. 8 ክፍል 2 ፤ ረስጣ 27 በደስ 7 በስ 48/ ።

ሐ/ አናጉንስጢስ ሚስት የላገባ ከሆነ ከሴት ርቆ እንደኖረ ካልተመሰከረለት አይሾምም /ፍት. መን. አን. 8 ክፍል 2/ ።

## 3/ የአናጉንስጢስ ሥራ

ሀ/ አናጉንስጢስ አንባቢ ስለሆነ በቤተ ክርስቲያን ያነብባል /ፍት. መን. አን. 8 ክፍል 3 ፤ ድስቅ 1 ቀዳማዊ/ ።

ለ/ አናጉንስጢስ ከፍ ከአለ ቦታ ቆሞ ከብሉያት መጻሕፍት በክፍል እየከፈለ እየመጠነ ያነብባል /ፍት. መን. አን. 8 ክፍል 3 ድስቅ 12/ ።

ሐ/ አናጉንስጢሳውያን ንባብ በሚያነቡበት ጊዜ ልብሰ ተክህኖ አይለብሱም /ፍት. መን. አን. 8 ክፍል 3/ ።

## 4/ አናጉንስጢስ የሚሻርበት ምክንያት

ሀ/ አናጉንስጢስ ከሰረቀ ከሹመቱና ከማንበብ ሥራው ይታገዳል ፤ ከዓመት በኋላ ግን ወደ ሥራው ይመለሳል ፤ ማዕርግ አይጨመርለትም ፤ እስከ ዕለተ ሞቱ ድረስ በአንባቢነቱ ማዕርግ ይኖራል /ፍት. መን. አን. 8 ክፍል 4 ፤ በስ 48/ ።

ለ/ በገና መቺ ከሆነ ከተሾመ በኋላ ወደዚህ ሥራው መመለስ አይገባውም ፤ ከተመለሰና በዚሁ ሥራው ከተገኘ በሰባት ሱባኤ ጾም ይቀጣል ፤ ካልታረመ ከቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ይለያል /ፍት. መን. አን. 8 ፤ ክፍል 4 በስ 74/ ።

### 5/ ሥርዓተ አናጉንስጢስ

አናጉንስጢስ ሚስት ማግባት ይችላል ፤ ሚስቱ ከሞተችበት ሁለተኛ ያገባል /ፍት. መን. አን. 8 ክፍል 5 ፤ ረስጠብ 117 በስ 55/ ።

## ሰ/ የመዘምራን ሢመት ሥርዓት

### 1/ ሥርዓተ ሢመተ መዘምራን

ኤጲስ ቆጶስ መዘምራንን በቡራኬ ይሾማል እንጂ እንብሮተ እድ አያደርግም /ፍት. መን. አን. 8 ክፍል 2/ ።

### 2/ የመዘምራን ሥራ

ሀ/ መዘምራን ዘማሪዎች ስለሆኑ ይዘምራሉ /ፍት. መን. አን. 8 ክፍል 3/

ለ/ መዘምራን የሚዘምሩት ከመዝሙረ ዳዊት ነው /ፍት. መን. አን. 8 ክፍል 3 ድስቅ 12/ በሀገራችን የቅዱስ ያሬድን ድርሰት ጭምር ይዘምራሉ ።

ሐ/ መዘምራን በሚዘምሩበት ጊዜ ልብሰ ተክህኖ አይለብሱም /ፍት. መን. አን. 8 ክፍል 3/

### 3/ ሥርዓተ መዘምራን

መዘምራን ሚስት ማግባት ይችላሉ ። ሚስታቸው ከሞተችባቸው ሁለተኛ ማግባት ይችላሉ /ፍት. መን. አን. 8 ክፍል 5 ፤ ረስጠብ 17 በስ 55/

## ሸ/ የዐጸውተ ኆኅው ሢመት ሥርዓት

### 1/ የዐጸውተ ኆኅው ሥራ

ሀ/ ዐጻውተ ኆኅው /ደጆች የሚከፍቱና የሚዘጉ/ በወንዶች መግቢያ በር ቆመው ይጠብቃሉ /ፍት. መን. አን. 8 ክፍል 3 ድስቅ 12/ ።

ለ/ ዐጻውተ ኆኅው አንዲት ሰዓት እንኳ ከበሩ መለየት የለባቸውም /ፍት. መን. አን. 8 ክፍል 3 ፤ ጸክ 49/ ።

ሐ/ ዐጻውተ ኆኅው ደሙን አያቀብሉም /ፍት. መን. አን. 8 ክፍል 3 ጸክ 39/ ።

2/ <u>ሥርዓተ ዐጸውተ ኀዋኀው</u>

ዐጸውተ ኀዋኀው ሚስት ማግባት ይችላሉ ሚስቶቻቸው ከሞቱባቸው ሁለተኛ ማግባት ይችላሉ ። /ፍት. መን. አን. 8 ፤ ክፍል 3 በስ 55/።

ቀ/ <u>የዲያቆናውያት ሢመት ሥርዓት</u>

1/ ለዲያቆናዊትነት ሢመት የሚያበቁ ሁኔታዎች፡-

ሀ/ በልባቸው ከኃጢአት የነጹ
ለ/ ለበጎ ሥራ የነቁ፥
ሐ/ በሥራው ሁሉ የሚታመኑ፥
መ/ ነገር የማይሠሩ
ሠ/ 60 ዓመት የሞላቸው፥
ረ/ በአንድ ወንድ ጸንተው የኖሩ
ሰ/ ልጆቻቸውን በሥርዓት ያሳደጉ
ሸ/ እንግዳ የሚቀበሉ
ቀ/ የቅዱሳንን እግር የሚያጥቡ
በ/ በደዌ ችግር ለተጨነቁት የሚራሩ
ተ/ በበጎ ሥራ ሁሉ ጸንተው የኖሩ

በበጎ ሥራ ጸንተው ለመኖራቸውም የተመሰከረላቸው ሴቶች ዲያቆናዊትነት ይሾማሉ /ፍት. መን. አን. 8 ክፍል 1 ፤ ድስቅ 17 ፤ 1ጢሞ. 5፡9-10/ ።

3/ <u>ሥርዓተ ሢመተ ዲያቆናውያት</u>

ዲያቆናውያት በአንብሮተ እድ አይሾሙም። የሚሾሙት በቃል ብቻ ነው /ፍት. መን. አን. 8 ክፍል 1 ድስቅ 17/ ።

4/ <u>የዲያቆናውያት ሥራ</u>

ሀ/ ዲያቆናውያት የሚሾሙት ከኤጲስ ቆጶሱ ወደ ሴቶች ለመላክ፥ የሚጠመቁትን ሴቶች ከአንገት በታች ቅብዕ ቅዱስ፥ ሜሮን እንዲቀቡ በጠቅላላ በሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን ሴቶች ሊፈጽሙት የሚገባውን የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት እንዲፈጽሙ ነው /ፍት. መን. አን. 8 ክፍል 1 ፤ ድስቅ 17 ረስጣ 59/ ።

ለ/ ዲያቆናውያት ሴቶች አይባርኩም ፤ ዲያቆናትና ቀሳውስት የሚሠሩትን የክህነት ሥራ አይሠሩም፥ ሴቶች የሚገቡበትን በር ብቻ ይጠብቃሉ /ፍት. መን. 8 ክፍል 3 ረስጣ 59/ ።

ሐ/ ዲያቆናውያት በሕዝቡ ዘንድ ክብር አላቸው "ወትኩን ዲያቆናዊት ክብርተ በኀቤክሙ" /ፍት. መን. አን. 8/ ።

መ/ ዲያቆናውያት እንደ ዲያቆናት "ተንሥኡ ጸልዩ" እያሉ ጸሎት አያዝዙም ፤ ዲያቆን ሳያዝዛቸውም ምንም ነገር አይሠሩም /ፍት. መን. አን. 8 ክፍል 3 በደስ 6/ ።

ሠ/ ስለማናቸውም ጉዳይ ለመነጋገር አንዲት ሴት ዲያቆናዊትን ሳትይዝ ብቻዋን ወደ ዲያቆን ወይም ወደ ኤጲስ ቆጶስ መሔድ አይገባትም ፤ ክልክል ነው /ፍት. መን. አን. 8 ክፍል 3 በደስ 6/ ።

ረ/ ዲያቆናዊት ሴቶችን ልትገሥፅ÷ ልትመክር÷ ልታስተምር በመሳሰለው ሁሉ ልትረዳቸው ይገባል /ፍት. መን. አን. 8 በደስ 34/ ።

ሰ/ ዲያቆናውያት ቅስና አይሾሙም ፤ ቄስ አይባሉም በቤተ ክርስቲያንም የማኅበር ጸሎት ጀማሪ÷ ፈጻሚ አይሆኑም ።

ቀ/ ዲያቆናውያት ቃላቸውን ከፍ አድርገው ጮኸው አይጸልዩም "ወኢይጸልያ በልዑል ቃል" /ፍት. መን. አን. 8 ክፍል 3 ጸክ 11/።

5/ <u>የክህነት ዓላማና ጥቅም</u>

የክህነት ዓላማና ጥቅም ሰዎችን ከኃጢአትና ከሰይጣን ሥራ ሁሉ በመለየት÷ በማስተማር÷ በመቆጣጠር÷ በመጠበቅ÷ በመቀደስና በማንጻት÷ በመናዘዝና በመፍታት፡-

ሀ/ ለጨለማው ዓለም ብርሃን ለመሆን÷

ለ/ አልጫ የሆነውን ዓለም ለማጣፈጥ÷

ሐ/ ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያንን በመፈጸም ለምእመናን ጸጋ መንፈስ ቅዱስን ለማሰጠት የእግዚአብሔር ልጆች÷ የመንግሥት ወራሾች እንዲሆኑ ለማብቃትና ድኅነተ ነፍስ ለማሰጠት ነው ።

መ/ እግዚአብሔርን በቅዳሴ በውዳሴ ለማመስገንና መንፈሳዊ አገልግሎት ለመፈጸም ነው ።

6/ <u>የሥርዓተ ክህነት ትርጉም</u>

ሀ/ ልጆቹን ሠርቶ ቀጥቶ ማሳደግ ያልቻለ ÷ በቤተሰብ አስተዳደር ያልተፈተነ በቤተ

ክርስቲያን ላይ እንዳይሾም የተከለከለበት ምክንያት ሠሪዐ ቤቱን ያላሳመረ ቤተሰብ ማስተዳደር ያልቻለ ፥ ቤተ እግዚአብሔርን ማስተዳደር ስለማይችል ነው ፡፡

"አመሰ ውእቱ ዘኢያሤኒ ሠሪዐቤቱ እፎ ያሤኒ ሠሪዐ ቤተ እግዚአብሔር ወቤተ ክርስቲያኑ" /1ኛ ጢሞ. 3፡4-5 ፤ ፍት. ነገ. 5/

ለ/ ሐዲስ አማኒ ኤጲስ ቆጶስነት እንዳይሾም የተከለከለበት ምክንያት ሰይጣን በአመጣው ትዕቢት እንዳይያዝና እንዳይታበይ ነው ፡፡

"በትዕቢት ተነፍቶ በዲያብሎስ ፍርድ እንዳይወድቅ አዲስ ክርስቲያን አይሁን" /1ኛ. ጢሞ. 3፡6 ፤ ፍት. ነገ. አን. 5፡9/

ሐ/ ዕውር ፥ ደንቆሮ ፥ ዝንጉ ኤጲስ ቆጶስነት እንዳይሾም የተከለከለው ነውር ሆኖበት አይደለም ፡፡ በቤተ እግዚአብሔር ከሚሠራው ሥራ እሱ ሊሠራው የሚገባውን ሥራ መሥራት የማይቻለው ስለሆነ ብቻ ነው ፡፡

"አኮ ከመ ውእቱ ነውር አላ እስመ ውእቱ ኢይክል በእንተ ፈጽሞቱ ለዘውእቱ ይትፈቀድ እምግብራተ ቤተ ክርስቲያን" /3ቀሌ አንቀጽ 52 ፤ ፍት. ነገ. አንቀጽ 5/ ፡፡

መ/ ኤጲስ ቆጶስ እሑድ እንዲሾም የተወሰነበት ምክንያት ሕዝቡ አምስቱን ቀን በተግባረ ሥጋ አሳልፈው ቀዳሚት በተግባረ ነፍስ ማለት ሰው በማስታረቅ፥ ሕሙማንን እሥረኞችን በመጠየቅ ውለው ለጸሎት፥ ሥጋ ወደሙ ለመቀበል ወደ ቤተ ክርስቲያን የሚሔዱትና የሚሰበሰቡት እሑድ ስለሆነ ሁሉ እንዲያውቀውና በሕዝብ ፊት እንዲሾም ነው ፡፡ ሁለተኛም እሑድ ጌታ የተጸነሰበት፥ ብርሃን መለኮቱን በደብረ ታቦር የገለጠበት ከሙታን ተለይቶ የተነሣበት መንፈስ ቅዱስ በሐዋርያት ላይ የወረደበት እመቤታችን ያረፈችበት ቅዱስ ዕለት ስለሆነ በቅዱስ ዕለት ቅዱስ ሢመት እንዲፈጸም ነው ፡፡ ከዚህም ሌላ "አምስት መክሊት ሰጥተኸኝ ነበር ወጥቼ ወርጄ ነግጄ አትርፌ አምስት ጨምሬበታለሁ እነሆ መክሊትህ ከነትርፉ" ብሎ ኤጲስ ቆጶሱ በኋላ የሚያስረክብባት ዕለት ስለሆነች ነው /ዘፀ. 20፡8-11 ፤ ማቴ. 28፡1 ፤ ማር. 16፡1-13 ፤ ሉቃ. 24፡1-43 ፤ ዮሐ. 20፡1-21 ፤ የሐ. ሥራ. 2፡1-21 ፤ ማቴ. 25፡14-23/ ፡፡

ሠ/ ኤጲስ ቆጶሳቱ በአንብሮተ እድ ኤጲስ ቆጶሱን ከመሾማቸው በፊት እጃቸውን የሚታጠቡበት ምክንያት እኛ በምናውቀው በአፍአ ንጹሕ ብለን ሾመንሃል ። አንተ በምታውቀው በውስጡ ዕዳ የለብንም ዕዳው በአንተ ነው ለማለት ነው ።

ረ/ ኤጲስ ቆጶሱን ሲሾሙት መስቀል የሚያሲዙት መከራ ትቀበላለህ ለማለት ነው ።

"ዘውእቱ ዘተሠይመ ለቤተ ክርስቲያን ጉባኤ እምነበ ሥሉስ ቅዱስ በምሥጢረ መስቀል" /ፍት. ነገ. አን. 5/

ሰ/ ቀዳማዊው ኤጲስ ቆጶስ በተሿሚው እድ ላይ እጁን የሚጭነው እስከ አሁን ድረስ ከእኔ በታች ነበርህ ከእንግዲህ ወዲህ ግን በሥልጣነ ክህነት ከእኔ ጋር አንድ ነህ ሲለው ነው ።

ሸ/ የሚመተ ኤጲስ ቆጶሳት በዓል ሦስት ቀን የሚከበረው ጌታችን መድኃኒታችን እየሱስ ክርስቶስ ሦስት መዓልት ሦስት ሌሊት በከርሠ መቃብር አድሮ በ3ኛው ቀን ከሙታን ተለይቶ የመነሣቱ ምሳሌ ነው ።

"ወያብዕሉ ሠለስተ መዋዕለ በዐለ መንፈሳዊተ በአምሳለ ምሥጢሩ ለዘተ ንሥአ በሣልስት ዕለት" /ፍት. ነገ. 5 ፤ ማቴ. 16፥21 /

ቀ/ ዲያቆናት በሚሾመው ኤጲስ ቆጶስ ራስ ላይ ፬ቱን ወንጌል ዘርግተው የሚይዙበት ምክንያት ወንጌልን ገልጠህ ታስተምራለህ÷ ስለ ወንጌል መከራ ትቀበላለህ ለማለት ነው ።

በ/ <u>መጀመሪያው የኤጲስ ቆጶሳት ጉባኤ</u> የርክበ ካህናት ዕለት እንዲሆን የተደረገበት ምክንያት ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ከትንሣኤው በኋላ 3ኛ ጊዜ በባሕረ ጥብርያዶስ ለደቀ መዛሙርቱ የተገለጠበት ቀን በመሆኑና በዚህም ዕለት ቅዱስ ጴጥሮስን ሊቀ ሐዋርያት አድርጎ በመሾም 3 ጊዜ በጎቼን ጠብቅ ብሎ የደቀ መዛሙርቱ የበላይና የምእመናን ጠባቂነት አደራ የሰጠበት ዕለት በመሆኑ ነው /ዮሐ. 21፥1-17/ ። <u>ሁለተኛው ጉባኤ</u> ጥቅምት 12 ቀን የሆነበት ምክንያት ይህ ዕለት መጀመሪያውን ወንጌል መንግሥት የጻፈው የሐዋርያው የማቴዎስ መታሰቢያ በዓል ከመሆኑም በላይ ወቅቱ ክረምቱ አልፎ በጋው የሚተካበት÷ አዝመራ የሚሰበሰብበት ጊዜ ስለሆነ በበጋም ችነፈርና ድንገተኛ ሞት ስለሚበዛ ከሞት

አስቀድሞ በፍቅር በንጽሕና ሆኖ ንስሐ ገብቶ በጸሎትና በምስጋና እግዚአብሔርን ለመለመን ነው ።

ተ/ በኤጲስ ቆጶሳት ጉባኤ /ሲኖዶስ/ መካከል በአለ ጠረጴዛ ላይ ወንጌል የሚቀመጥበት ምክንያት በጉባኤው መካከል ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አለ ለማለትና እውነተኛ ፍትሕ እንፈርዳለን በጽድቅ እንነጋገራለን ለማለት ነው ።

ቸ/ ዲያቆን በ30 ዓመቱ ቅስና እንዲሾም የተደረገበት ምክንያት ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በ30 ዓመቱ ስለተጠመቀና ማስተማር የጀመረው በዚሁ ዘመኑ ስለሆነ ነው /ሉቃ. 3፡23 ፤ ፍት. ነገ. አን. 6፡1/ ።

ኀ/ ብሉያትን ሐዲሳትን ይልቁንም አራቱን ወንጌል ያልተማረ ቅስና እንዳይሾም የተከለከለበት ምክንያት ምእመናንን ትምህርተ ወንጌል እያስተማረ የሚጠብቅ ስለሆነ ነው ።

ነ/ ኤጲስ ቆጶስ ቄሱንና ዲያቆኑን ብቻውን የሚሾመው መዓርጉ 3ኛ/ ስለሆነ ነው ። ይኸውም ወደላይ ጳጳስ ፥ ሊቀ ጳጳሳት ፥ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ፥ ወደታች ቄስ ዲያቆን ነው ።

ኘ/ ካህን ሁለት እኅትማማች ከአገባ ሰው ሠርግ እንዳይሔድ የተከለከለበት ምክንያት ጋብቻው ሕገወጥና ርኩስ ከመሆኑም በላይ ሠርገኛውም ኃጢአተኛ ስለሆነ ነው ።

አ/ ዲያቆን ለካህናት ሥጋውን ደሙን የማያቀብልበት ምክንያት እሱ የካህናት ተላላኪ እንጂ ካህን ስለ አልሆነ ነው ።

"ወኢየሀብ አውሎግያ አላ ውእቱ ይነሥእ እምኤጲስ ቆጶስ ወእምቀሲስ ወኢይፀር ቁርባነ ወሰበ ያረ ኤጲስ ቆጶስ አው ቀሲስ ውእቱ ይመጡ ፅዋዐ ለሕዝብ አኮ ውእቱ ካህን አላ ላእከ ካህናት" 1ኛ/ ቀሌ 58 ፍት. ነገ. አን. 7 ክፍል 3/ ።

"ወኢየንብር እዴሁ ወኢይመጡ ቁርባነ ለዘይትሌዓሎ አላ የአኃዝ ዘይቴሐትዎ ለመልእክተ ቤተ ክርስቲያን" /ቀኖና ጴጥሮስ/

ከ/ ሊቀ ዲያቆናት ለኤጲስ ቆጶሱ የአስተዳደር ሥራ ረዳት እንዲሆነውና ጥቃቅኑን ሥራ እንዲያከናውን የተደረገበት ምክንያት በአራቱ በእሥራኤል ልጆች መካከል ስለሚፈርደው ፍርድ

ሥራ እንዳይበዛበት ሥልጣኑን እንዲያከፋፍል አማቱ ዮቶር ሙሴን እንደመከረው ሙሴም ምክሩን ተቀብሎ ሥልጣኑን በማከፋፈል ሥራ እንደተቃለለለትና ፍጻሜው እንደ አማረለት ሁሉ ኢጲስ ቆጶሱም ሥልጣኑን ከአከፋፈለ የቤተ ክርስቲያን ሥራ ሊቃለልና ባለ ጉዳዮች በቀላሉ ውሳኔ ሊያገኙ እንደሚችሉ ስለታመነ ነው ። "ከመ ይኩን ዘኢያስተሐምም ዘእንበለ ግብራት ዓቢያን በከመ አምከሮ ዮቶር ሐሙሁ ለሙሴ በእንተ ሠሪዐ ፍትሕ ማእከለ ደቂቀ እሥራኤል ወተወከፈ ምክረ ዚአሁ ወአሠነየ ደኅሪተ" /ፍት. ነገ. አን. 7 ክፍል 4 ፤ ዘፀ. 18፡13-26/ ።

ኸ/ አናጉንስጢስ ከብሉያት መጻሕፍት ሁለት ሁለት ክፍል የሚያነብበት ምክንያት አንዱ የዊዋዌ ሥጋና የዊዋዌ ነፍስ÷ አንዱ የሚጠተ ሥጋና የሚጠተ ነፍስ ምሳሌ ነው ። /2ኛ/ ዜና መዋ. 36፡5-23 ፤ ዕዝ. 1፡1-7 ፤ ማቴ. 1፡11-12 ፤ ዘፍ. 3፡1,24 ፤ ዮሐ. 3፡14,18 ፤ 1ኛ. ጴ. 3፡19/ ።